# ኳታር እና ኢትዮጵያ በሶማልያ ጉዳይ ለምን ተጣሉ?

አብይ ጨልቀባ*

ይሂን ፅሑፍ ለመፃፍ ያስገደደኝ አንደኛዉ ሙያየ ስለሆነ፣ ሁለተኛዉ ማንም ሊያዉቀዉ የሚገባ ያገር ጉዳይ ስለሆነ ነዉ፡፡ የኳታር ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት ልዑክ ከኢትዮጵያ አቻው ጋር በብሔራዊ ቤተ መንግሥት ውይይት ማካሄዱ ሰምተናል፡፡የኢትዮጵያ መንግሥት በወቅቱ ግንኙነቱን ለማቋረጥ የወሰነው ኳታር የሶማሊያ አሸባሪዎችን በመርዳት፣ የአፍሪካ ቀንድን የመረበሽና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ደኅንነት ላይ ጉዳት የማድረስ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ነች በማለት ወቀሳውን ከሰነዘረ በኋላ ነው፡፡ ይሄ እንደተጠበቀ ሁኖ መንግስት ጉዳዩን ሙያ በልብ በሚል መንፈስ ጉዳዩን ግንኙነት ከማቋረት ዉጭ የተነፈሰዉ ጉዳይ አልነበረም፤ የኳታር መንግሥት የኢትዮጵያን ወቀሳ መሠረተ ቢስ ውንጀላ ነው በማለት ቢያስተባብልም፤ የዚህ ፅሑፍ ዋና አላማ የኢትዮጵያን መንግስት ወቀሳ በመረጃ እና ማስረጃ ለማስደገፍ ነዉ፡፡ ሁለተኛዉ አላማ ደግሞ በሶማልያ ጉዳይ የኳታር መንግሥት የፓለቲካ ባህሪ ለዉጥ በግዴታ እንጂ በዉዴታ እንዳልመጣ ማስረዳት ነዉ፡፡ በሶማሊያ የተገኘውን አንፃራዊ ሰላም ለማጐልበትና አገሪቱን በድጋሚ ለመገንባት የኳታር መንግሥት ለዚህ ልዩ ድጋፍ ለመስጠት የተስማማዉ ተገዶ እንጂ ፈልጎ እንዳልሆነ ለማስረዳት ጭምርም ነዉ፡፡ ለዚህ ፅሑፍ ለማዘጋጀት ከታሪካዊ መፃህፍቶች እስከ የዊኪሊክስ መረጃዎች ተጠቅሚያለዉ ፡፡ መልካም ንባብ፡፡

የፀብ መጀመርያ እ.ኤ.አ በ2006 ዓ.ም የእስላማዊ ፍርድ ቤት ህብረት ተብሎ የሚጠራዉ ፣ የሶማልያን ቦታዎች ሙሉ በሙሉ በመቆጣጠር፣ አለም አቀፍ እዉቅና የተሰጠዉ ግን ደካማ የነበረዉ የባይድዋ መንግስት ተብሎ የሚጠራ የአሁኑ የሶማልያ መንግስት መሰረት የሆነዉ ለማጥቃት እና ለማጥፋት በተንቀሳቀሰበት ወቅት ነበር፡፡ ከዚህ ባለፈ በተመሳሳይ ኢትዩጵያ ላይ “የሃይማኖት ጦርነት” ያወጀበት ወቅት ጭምር ነበር፡፡ የእስላማዊ ፍርድ ቤት ህብረት የአክራሪ እስልምና አጀንዳ ይዞ የሚንቀሳቀስ እና በአንዳንድ የዉጭ አገራት እየተደገፈ መንግስት ለማቋቋም ዳር ደርሶ የነበረ ሃይል ነበር፡፡ ከእስላማዊ ፍርድ ቤት ህብረት የኢኮኖሚና የዲፕሎማሲያዊ ድጋፉ

*አቶ አብይ ጨልቀባ በአምቦ ዩኒቨርስቲ መምህር ናቸዉ፡፡ በኢሜይል አድራሻቸዉ chewabiy@gmail.com ማግኘት ይቻላል፡፡

በስተጀርባ የነበሩት የዉጭ መንግስታት በቀዳሚነት የሚጠቀሱት ኳታር እና ኢራን ነበሩ፤ የተለያየ የፓለቲካዊ እስልምና ፍልስፍና የሚያራምዱ ቢሆንም ፡፡ የእስላማዊ ፍርድ ቤት ህብረት ሶማልያን ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል የተቆጣጠረበት ወቅት፣ የተባበሩት መንግስታት በሶማልያ ለሁለት አስርት አመታት ጥሎት የነበረዉ የጦር መሳርያ ማዕቀብ በሰፊዉ እየተጣሰ የነበረበት ጊዜ ነበር፡፡ እ.ኤ.አ በግንቦት 2006 ዓ.ም የተባበሩት መንግስታት ቋሚና እና ጊዚያዊ የፀጥታዉ ምክር ቤት አባላት ለምሳሌ ቻይና፣ጃፓን፣ ግሪክ፣ ሩስያ፣ኮንጎ እና ጋና የጦር መሳርያ ማዕቀብ መጣሱ የተቋወሙ ሲሆኑ፣ ጠበቅ ያለ ቁጥጥር እና ክትትል እንዲደረግ አጥብቀዉ ጠይቀዋል፡፡ በዚያን ወቅት የሶማልያ የጦር መሳርያ ማዕቀብ ተቆጣጣሪ ኮሚቴ ሊቀ መንበር ኳታር ነበረች፡፡ የኳታር መንግስት እንደ ሊቀመንበርነቱ አዎንወታዊ ሚና መጫወት ትቶ፣ ፀረ ኢትዩጵያ የሆኑ አቋሞች ባገኘችዉ አጋጣሚ መጠቀም ስራየ ብሎ ተያያዘዉ፡፡ ኳታር የሶማልያ የጦር መሳርያ ማዕቀብ ተቆጣጣሪ ኮሚቴ ስራ ለማቀላጠፉ ቃል ገብታ የነበረች ብትሆንም፣ የጦር መሳርያ ማዕቀብ ጥሰት አይታ እናዳላየች፣ ሰማታ እንዳልሰማች በዝምታ የሚገለፅ አፍራሽ የሆነ ግዳጅ ይዛ ስትንቀሳቀስ የነበረችዉ፡፡

እ.ኤ.አ በግንቦት 2006 ዓ.ም የእስላማዊ ፍርድ ቤት ህብረት ሶማልያን ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር እየተንቀሳቀ የነበረበት እንዲሁም የሚያካሂደዉ ዘመቻ ያጠናከረበት በነበረበት ወቅት ፣ ኳታር የባይድዋን መንግስት ከልብ ሳትቀበለዉ ግን የእርስ በእርስ ጦርነት አቁሞ ሁሉም ወገኖች ወደ ድርድር እንዲገብ ከሌሎች የፀጥታዉ ምክር ቤት አባላት ጥሪ አቅርባ ነበር፤ ከልብ የመነጨ ባይሆንም፡፡ የዚህ ሁሉ ድራማ መቋጫ ያገኘዉ በኢትዩጵያ መከላከያ ሰራዊት ጣልቃ ገብነት እንደነበረ የቅርብ አመት ትዉስታ ነዉ፡፡ ከዛ ብኃላ የባይድዋን መንግስት በአብዱላሂ የሱፍ መንግስት አመራር እና በኢትዩጵያ መንግስት ድጋፍ እየተጠናከረ የሄደበት ሂደት መጣ፡፡ በዚህ ወቅት ኳታር የተባበሩት መንግስታት ጊዝያዊ የፀጥታ ምክር ቤት አባል በነበረችበት ወቅት( እ.ኤ.አ 2006-2007 ዓ.ም ) የሶማልያ ጉዳይ በተነሳ ወቅት የኢትዩጵያ ሰራዊት ያለ ቅድመ ሁኔታ ከሶማልያ መዉጣት አለበት ብላ ሽንጧን ገትራ ስትከራከር የነበረች አገር ነች፡፡

ከአንድ አመት ብኃላ እ.ኤ.አ ግንቦት በ2007 ዓ.ም የባይድዋን መንግስት የፓርላማ አባላት የነበሩ ወደ 42 የሚጠጉ ተወካዮች በአብዱላሂ የሱፍ የሚመራዉን መንግስት በመቃወም ፣ "የሶማልያ ነፃ ፓርላማ" ራሱን በማለት ከሶማልያ ዉጭ ወጥተዉ ለብቻቸዉ የሚንቀሳቀሱበት ጊዜ ነበር፡፡ "የሶማልያ ነፃ ፓርላማ" ከአስመራ እና ኳታር

መንግስታት ጠበቅ ያለ ግንኙነት የመሰረተበት ወቅት ጭምር ነበር፡፡ “የሶማልያ ነፃ ፓርላማ” መቀመጫዉ አስመራ አድርጎ በቀድሞ የፓርላማ አፈ-ጉባኤ ሻሪፍ ሃሰን ሼኽ አዳን የሚመራ ቡዱን ነበር፡፡ “የሶማልያ ነፃ ፓርላማ” የፓለቲካ ግብ በወቅቱ የሶማልያ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት ጌዲ በለዘብተኛ የእስላማዊ ፍርድ ቤት ህብረትአባል ተተክቶ፣ ለሃዊይ ጎሳ አባል የጠቅላይ ሚኒስተርነቱ ቦታ እንዲሰጠዉ ነበር፡፡ “የነፃ ፓርላማ” ቡዱን የመጨረሻዉ ግብ ግን በአብዱላሂ የሱፍ የሚመራዉን መንግስት ማስወገድ እንደነበረ ለማንም ግልፅ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት የኳታር መንግስት ሌላ ጥፋት ሰራ፡፡ በአብዱላሂ የሱፋ የሚመራዉን መንግስት ወደ ጎን በመተዉ ፣ ሻሪፍ ሃሰን ሼኽ አዳን እና የእስላማዊ ፍርድ ቤት ህብረት ለዘብተኛ የነበሩ ኃላም የሶማልያን ፕሬዝደንት የሆኑት ሼኽ ሸሪፍ ሼኽ አህመድ በኳታር ዶሃ ለማደራደር ጥረት አድርጋለች፡፡ ኳታር ሻሪፋ ሃሰን ሼኽ አዳን እና ሼኽ ሸሪፋ ሼኽ አህመድ ለማደራደር እንደ ምክንያትነት የተጠቀመችበት ፣ ሁለቱም ወገኖች “የኢትዩጵያ ሰራዊት ያለ ቅድመ ሁኔታ ከሶማልያ መዉጣት አለበት” የሚል ጊዝያዊ የፓለቲካ አቋም ነበር፡፡ ድርድሩ ግን ዉጤት አልባ ነበር፡፡ ምክንያቱም ለዘብተኛ የሆኑት የእስላማዊ ፍርድ ቤት ህብረት አባለት የሚኒስትርነት ቦታ ይዘዉ በአብዱላሂ የሱፋ የሚመራዉ መንግስት ለመቀላቀል አማራጭ ሃሳብ ያቀረቡት ሻሪፍ ሃሰን ሼኽ አዳን ኳታር ደስተኛ ባለመሆና ነበር፡፡

እ.ኤ.አ 2007 ዓ.ም ፀረ-ኢትዩጵያ የሚያራምዱ የነበሩት “የነፃ ፓርላማ” ብዱን እና የእስላማዊ ፍርድ ቤት ህብረት ሊቀ መንበር የነበሩት ሼኽ ሸሪፍ ሼኽ አህመድ እንዲሁም የፌደራል የሽግግር መንግስት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስተር የነበሩት ሁሴን መሃመድ ፍራ አይዲድ በኤርትራ መንግስት ጋበዥነት አስመራ ላይ እንዲገናኙ ኳታር ከኤርትራ መንግስት በስተጀርባ ሁና ስትንቀሳቀስ ነበር፡፡ የኤርትራ መንግስት ምኞት የሞቃድሾን መንግስት ሊቀናቀን የሚችል ሌላ መንግስት እንዲቋቋም ነዉ፡፡ ለዚህ ተግባር እንዲደርስ የኢትዮ-ኤርትራ የድንበር ዉሳኔ አፈፃፀም ላይ ቅሬታ በማሳደሩ ነዉ፡፡ የኤርትራ መንግስት የኢትዮ-ኤርትራ የድንበር ዉሳኔ ያለ ቅድመ ሁኔታ እንዲፈፀም ፋላጎቱ ነዉ፡፡ የኢትዮ-ኤርትራ የድንበር ዉሳኔ ተፈፃሚነት ዋስ የሆኑት የአሜሪካ እና የአልጀርያ መንግስታት ኢትዩጵያን ማስገደድ ባለ መቻላቸዉ የኤርትራ መንግስት ቅሬታ እንዳደረበት የምስራቅ አፍሪካ ተንታኞች ይገልፃሉ፡፡ ኤርትራም የፀረ ኢትዩጵያ ሃይሎች ማደራጀት የዚህ ቅሬታ ዉጤት ነዉ፡፡በኢትዮ-ኤርትራ የድንበር ዉሳኔ በተመለከተ የኳታር መንግስት በኤርትራ መንግስት የነበረዉ አቋም ተመሳሳይ ነበር፡፡

የኳታር መንግስት በኢትዩጵያ የዉስጥ ጉዳይ ጭምር ገብታል፡፡ የቀድሞ የእስላማዊ ፍርድ ቤት ህብረት አባል የነበሩት እና የኢትዩጵያ የሽብርተኝነት ዝርዝር ዉስጥ የገቡት አዳን ሃሺ ኤይሮ ያደረገችዉ ቀጥታዊ ያልሆነ ድጋፋ ነዉ፡፡ አዳን ሃሺ ኤይሮ በኢትዩጵያ ሶማልያ የሚንቀሳቀስ ራሱ ኦብነግ ብሎ የሚጠራዉ ኃይል ጋር በመመሳጠር ፀረ ሰላም የሆኑ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ነበር፡፡

እ.ኤ.አ ሐምሌ 2007 ዓ.ም ሶማልያ በታሪካ ትልቅ የሚባል ታሪካዊ ሂደት አስተናግዳለች፡፡ እሱም የሶማልያ ሙሉ ጎሳዎች ሊባል በሚችል የተካፈሉበት የእርቅ እና የሰላም ኮንፈረንስ ነበር፡፡ የሶማልያ የእርስ በርስ ጦርነት ምክንያት እስከ የንብረት እና ሀብት ክፍፍል የሚመለከት ለ45 ቀናት የቆየ ኮንፈረንስ ነበር፡፡ እ.ኤ.አ 1991 ዓ.ም የሶማልያ የእርስ በርስ ጦርነት ለመጀመር ምክንያት የነበሩ የሃዊይ ጎሳዎች ተሳትፈዉ ነበር፡፡ የሃዊይ ጎሳዎች ንኡስ ጎሳዎች እንደ ኡጋስ ሃዋድል፣ ኡጋስ ዲር፣ ሱልጣን ሱሉዕማን፣ ሱልጣን ሙርሳድ በኮንፈረንሱ ተሳታፊዎች ነበሩ፡፡ ኮንፈረንሱ ላይ ያልተሳተፉት የሃዊይ ንኡስ ጎሳ ኡጋስ አይር ነበሩ፡፡ በአሜሪካ የሽብርተኝነት ዝርዝር ዉስጥ የገቡት ሃሰን ዳሂር አወይስ የሃዊይ ንኡስ ጎሳ ኡጋስ አይር በእርቀ ሰላሙ እንዳይሳተፉ ከፍተኛ ጫና በማሳደሩ እንደ ነበረ በምክንያትነት ይጠቀሳል፡፡ የእርቀ ሰላሙ የሃዊይ ንኡስ ጎሳ ኡጋስ አይር ባለ ማሳተፉ ግን ሙሉ በሙሉ ዉጤታማ ነበር ማለት አይቻልም፡፡ ሃሰን ዳሂር አወይስ በስተጀርባ ደግሞ የኤርትራ እና የኳታር መንግስታት ነበሩ፡፡

የሱዑዲ አረብያ ንጉስ አብደላሂ በአስመራ የሚገኘዉ የነበረ ቡዱን ወደ ሽግግር መንግስት እንዲገብ እንዲሁም ለዘብተኛ ተብለዉ የሚጠሩ የእስላማዊ ፍርድ ቤት ህብረት አባለት የኳታር መንግስት እንዲያግባባ ለቀረበላት ጥያቄ ፋቃደኛ አልነበረም፡፡ ሌሎች የኳታር ወዳጅ አገሮች በተደረገ የማግባባት ጥረትም ስኬታማ አልነበረም፡፡ ለምሳሌ የፈረንሳይ ከኳታር መንግስት ጥሩ ግንኙነት ካላቸዉ የአዉሮፓ አገራት አንዷ ነች፡፡የኳታር ኢሚር ልጅ በፈረንሳይ የጦር ኮሌጅ እንደሚማር እንዲሁም የሴት ጓደኛዉ የፕሬዝዳንት ነበር ሳርኮዚ እህት መሆና ኳታር ላይ ተፅእኖ ማሳደር ሞክራ ነበር፡፡ዉጤት አልባ ሆነ እንጂ፡፡

አሜሪካ ሌላዋ የኳታር ወዳጅ አገር ነች፡፡ግን አሜሪካ እና ኳታር በሶማልያ የነበራቸዉ አቋም የተለያየ ነበር፡፡አሜሪካ በሶማልያ ያላት አቋም ከሁለት አመክንየቶች ይመነጫል፡፡ መጀመርያዉ የፀረ-ሽብርተኝነት ትግል ሲሆን ሁለተኛዉ ደግሞ የነዳጅ ሕግ ጋር የተያያዘ ነዉ፡፡ የአሜሪካ የፀረ-ሽብርተኝነት ትግሉ እንደተጠበቀ ሁኖ እ.ኤ.አ

ከ 1991 ዓ.ም በፊት በሶማሊያ ነዳጅ ፋሊጋ የተሰማሩ የአሜሪካ ታላላቅ ኩባንያዎች ዉል እንዲቀጥል ትልቅ ፋላጎት አላት፡፡ አሜሪካ የአብዱላሂ የሱፋ እንዲሁም ሼኽ ሸሪፋ ሼኽ አህመድ መንግስት ድጋፍዋ የሰጠችዉ እ.ኤ.አ ከ1991 ግ.ም በፊት የነዳጅ ፍሊጋ ዉሎች እንደሚያከብሩ ቃል ስለ ገቡ ጭምር ነዉ፡፡ እ.ኤ.አ 1991 ዓ.ም በፊት በሶማሊያ የነዳጅ ፍሊጋ ዉሎች ዋና ተጠቃሚዎች የአሜሪካ ኩባንያዎች ናቸዉ፡፡

የኤርትራ መንግስት በሶማሊያ የዉስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባት ትርጉም እንዲኖረዉ ምክንያት የነበረችዉ ኳታር ነበረች፡፡ ምክንያቱም የኤርትራ መንግስት ለሶማሊያ አሸባሪ ቡዱኖች የሚያደርገዉ ድጋፍ የኤርትራ መንግስት ኢኮኖሚ የመሸከም አቅም የለዉም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ፀረ-ኢትዮጵያ አቋም ያላቸዉ ሃይሎች ድጋፍ ለማድረግ የኤርትራ መንግስት ኢኮኖሚ የመሸከም አቅም የለዉም፡፡ የኤርትራ መንግስት ከሱዳን ጀምሮ እስከ መካከለኛዉ ምስራቅ ጣልቃ ገብነት የኤርትራ መንግስት ኢኮኖሚ የመሸከም አቅም የለዉም፡፡ ለዚህም ኳታር በተዘዋዋሪ ተጠያቂ ነች፡፡

እ.ኤ.አ መስከረም 2007 ዓ.ም ኳታር በሚስጥር ራሱን "የሶማሊያ ዳግም ነፃ አዉጪ ህብረት" ብሎ የሚጠራዉ የአብዱላሂ የሱፍ መንግስት መተካት አላማ አድርጎ የተንቀሳቀሰዉ ቡዱን የቅድመ ድርድር ያካሄደዉ በኳታር ዋና ከተማ ዱኃ ላይ ነበር፡፡ "የሶማሊያ ዳግም ነፃ አዉጪ ህብረት" የኳታር መንግስት ፋላጎት የሚወክል እንደነበረ ግልፅ ነበር፡፡ ግን "የሶማሊያ ዳግም ነፃ አዉጪ ህብረት" በአንድ ድምፅ አቋም ይዘዉ እንዲሄዱ የኳታር እና የኤርትራ መንግስት ያደረጉት ጥረት የተሳካ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም "የሶማሊያ ዳግም ነፃ አዉጪ ህብረት" ስብስብ ጤናማ አልነበረም፡፡

ሌላ አግራሞት የፈጠረዉ ሂደት ግን ኳታር ሃሰን ዳሂር አወይስ ከአሜሪካ የሽብርተኝነት ዝርዝር እንዲሰረዝ በዉጭ ጉዳይ ሚኒስተር አህመድ አል ማሁሙድ በኩል ያደረገችዉ ዉጤት አልባ ሙከራ ነበር፡፡ ኳታር ሃሰን ዳሂር አወይስ ከአሜሪካ የሽብርተኝነት ዝርዝር ተሰርዞ የሶማሊያ መንግስት አካል እንዲሆን ትልቅ ፋላጎት ነበራት፡፡ ሃሰን ዳሂር አወይስ በተመለከተ የኳታር መንግስት ከኤርትራ መንግስት በጋራ ለመስራት ፋላጎት እንደነበራት መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

በስተመጨረሻም እ.ኤ.አ መጋቢት 2009 ዓ.ም የአረብ ሊግ አመታዊ ስብሰባ በኳታር ዋና ርእሰ ከተማ ዶኃ ላይ ነበር የተካሄደዉ፡፡ ለስብሰባዉ ከተያዙት የመወያያ አጀንዳዋች አንዱ የሶማሊያ መልሶ ለማቃቃም የአረብ ሊግ ሊያደርገዉ የሚገባ የገንዘብ ድጋፍ ነበር፡፡ ለዚህ ጉዳይ በሶማሊያዉ ፕሬዝደንት ሼኽ ሸሪፍ ሼኽ አህመድ ያደረጉት

ጥረት ፋሬ እንዳያፈራ እና የአረብ ሊግ አባል አገራት እንደ ህብረት ድጋፍ እንዳያደርጉ ዉስጥ ለዉስጥ ከፍተኛ የዲፕሎማሲያዊ ጨዋታ አድርጋለች፡፡ ለዚሁም ኳታር ተሳክቶላታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ኳታር የአፍሪካ ህብረት ጥበቃ ድጋፍ ተልእኮ በሶማልያ (AMISOM) ድጋፍ ለማድረግም ፍላጎት አልነበራትም፡፡

ስለሆነም ከአቅሙ በላይ የሆነበት የኢትዮጵያ መንግስት ያለዉ ቅሬታ ለኳታር መንግስት በተደጋጋሚ በተለያዩ አለም አቀፍ መድረኮች ያመለከተ ቢሆንም፣ የኳታር መንግስት ግን ከድሪጊቱ ሊቆጠብ አልቻለም ነበር፡፡ ስለሆነም በኢትዮጵያ እና በኳታር መንግስታት የዲፕሎማሲ ግንኙነት መቋረጥ ነበረበት፡፡ ስለሆነም ግንኙነቱ ተቋረጠ፡፡

ታድያ የአሁኑ የኢትዮጵያ እና የኳታር መንግስታት የዲፕሎማሲ ግንኙነት መሻሻል ለብቻዋ የተነጠለችዉን ኤርትራ ላይ ያለዉ ትርጉም ምንድን ነዉ ብሎ መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡ እርግጥ ነዉ የኳታር እና የኤርትራ መንግስታት በሶማልያ ያላቸዉ አቋም አሁን ተለያይቷል፡፡ ለዚህም ይመስላል የኤርትራ መንግስት በኳታር በኩል በአሁኑ በሃሰን ሼክ መሃሐድ የሚመራዉ መንግስት መታረቅ የፈለገዉ፡፡ ዉጤቱ በተቃራኒዉ ቢሆንም፡፡ ይሂ ሲባል ግን በሶማልያ ዉጭ ሁለቱም አገራት የሚያስተሳስራቸዉ የጋራ አጀንዳዎች ግን የሉም ማለት አይደለም ፡፡ ለምሳሌ የኤርትራ ወደቦች አስተዳደር፣ የዳህላክ ደሴቶች እንቨስትመንት፣ የአፍሪካ ቀንድ የፀጥታ እና ሰላም ጉዳዮች ኳታር እና ኤርትራን በጋራ የሚያስተሳስራቸዉ አጀንዳዎች ናቸዉ፡፡ የኳታር መንግስት በአፍሪካ ቀንድ እንዲሁም በምስራቅ አፍሪካ ለሚኖረዉ ተፅእኖ የኤርትራ ድጋፉ ይፈልጋል፡፡ኳታር ከኢትዮጵያ ጋር በብዙ ሁኔታዋች የጋራ አቋም መዉሰዱ ብቻ ኳታር በምስራቅ አፋሪካ ጉዳዮች የበላይ ሊያደርጋት አይችልም፡፡ አደራዳሪ የጠፋበት የኢትዮ-ኤርትራ የድንበር ዉሳኔም ለኳታር በቀንድ አፋሪካ የመጫወቻ ካርድ ሊሆን ይችላል፡፡በሶማልያ ያጣችዉ የዲፕሎማሲ ድል በየኢትዮ-ኤርትራ የድንበር አተገባበር ዉሳኔዉ በማስፈፀም ልታካክሰዉ ትችላለች፡፡

## ማጠቃለያ

የኳታር እና የኢትዪጵያ የሁለቱየሽ ግንኙነት መበላሸት የጀመረዉ የኳታር መንግስት በሶማልያ ጉዳይ ሲያራምደዉ በነበረዉ አቋም ምክንያት ነበር፡፡ የኳታር መንግስት የሶማልያ ጉዳይ በተመለከተ የሚያራምደዉ አቋም ከጅምሩ የተሳሳተ ነበር፡፡ የኳታር መንግስት የሶማልያ ጉዳይ የአፍሪካ አገሮች እና የአፍሪካ ህብረት አጀንዳ መሆኑን

ቀርቶ የአረብ ሊግ ጉዳይ እንዲሆን ተደጋጋሚ ዉጤት አልባ ሙከራዎች አድርጓል፡፡ እ.ኤ.አ 2006 እስከ 2008 ዓ.ም ሶማልያን ሲያስተዳድር የነበረዉ የሽግግር ፌደራላዊ መንግስት እዉቅና እንዳያገኝ በፊት አዉራሪነት ዘመቻዉ መርታለች፡፡ ኳታር የአብዱላሂ የሱፍ መንግስት የአረብ ሊግ አገሮች እዉቅና እናዳያገኝ ሌት ተቀን ሰለቸኝ ደከመኝ ሳትል ሰርታለች፡፡ የአረብ ሊግ ተፅእኖ ፈጣሪ አገሮች እንደ ሳዉዲ አረብያ የአብዱላሂ የሱፍ መንግስት እዉቅና እንዳይሰጠዉ የኳታር ጠቅላይ ሚኒስተር ሃሚድ በግል ሳእዉዲ አረብያ ንጉስ አብደላህ ለማግባባት ሞክሮ ሳይሳካለት ቀርቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የግብፅ መንግስት በሶማልያ የነበረዉ አቋም ከኳታር መንግስት የሚመሳሰል የነበረ ቢሆንም በስተመጨረሻ ግን የአብዱላሂ የሱፍ መንግስት እንደደገፈ ለማዎቅ ተችላል፡፡ስለዚህም የኳታር መንግስት የግብፅ መንግስት ለማግባባት ያደረገዉ ጥረት አልተሳካለትም፡፡ ስለሆነም የኳታር መንግስት በሶማልያ ያራምድ የነበረ አቋም የተሳሳተ እንደነበር ብዙ ተከታዪች አለማፍራቱ አንድ መገለጫ ነዉ፡፡

የኳታር መንግስት የሶማልያ ጉዳይ እሱ በሚፈልገዉ መንገድ ሳይሄድ ሲቀር የሞቃድሾዉ እና የአስመራዉ ቡዱን ለማግባባት በመሞከር ዶሃ ሌላ መደራደርያ ፎረም እንዲሆን ጥረት አድርጓል፡፡ የሶማልያ ጉዳይ የኢጋድ እና የአፍሪካን ህብረት አጀንዳ እንዳይሆን ብዙ ዉጤት አልባ ሙከራዎች አድርጋለች፡፡ የሶማልያ የቂም በቀል ጉዳይ አደብ ገዝቶ እርቀ ሰላም እንዲወርድ በሙሉ የሶማልያ ጎሳዋች የተሳተፉበት የ2007 እ.ኤ.አ በሞቃድሾ የተደረገዉ የሰላም ኮንፈረስ እዉቅና በመንፈግ የአስመራ ቡዱን ተብሎ የሚጠራ የፀረ-ኢትዩጵያ አቋም የሚያራምዱ የእስላማዊ ፍርድ ቤት ህብረት እዉቅና ሰጥታት ነበር፡፡ ከዚህ ባለፈ የኳታር መንግስት በኢትዩጵያ ዉስጣዊ ጉዳይ ከመግባትም አልቦዘነም፡፡ ፀረ-ኢትዩጵያ አቋም ያለዉ ራሱን "የኦጋዴን ነፃ አዉጭ ግንባር" ብሎ የሚጠራ አሸባሪ ቡዱን በኤርትራ በኩል ግንኙነት በመመስረት ኢትዩጵያ ላይ የእጅ አዙር ጦርነት ከፍታ ነበር፡፡ የአሸባሪዉ "የኦጋዴን ነፃ አዉጭ ግንባር" ፕሮፓጋንዳ የአለም አቀፍ አጀንዳ እና እዉቅና እንዲሰጠዉ በማሰብ ኳታር በዋናነት የምታንቀሳቅሰዉ የአልጀዚራን ቴሌቭዥንን በመሳሪያነት በመጠቀም ስፊ ሽፍን እንዲሰጠዉ በማድረግ ኢትዩጵያ ላይ የስም ማጥፋት ጦርነት ከፍታ ነበር፡፡ የአሜሪካ መንግስት የኳታር መንግስት ፀረ-ኢትዩጵያ አቋም እያወቀ ተፅእኖ ለማድረግ አለመሞከሩ ወይም አለመፈለጉ እንቆቅልሽ ነበር፡፡ ከኳታር መንግስት ቀረቤታ የነበራቸዉ አገራት እንደ ፈረንሳይ እና ጣልያን የኳታር የአፍሪካ ቀንድ አፋራሽ አካሄድ ለማስቆምም ፍላጎታቸዉ ከትንሽ ጥረቶች በስተቀር እምብዛም አልነበረም፡፡

የኳታር በተባበሩት መንግስታት የሶማልያ የመሳርያ ማዕቀብ ተቆጣጣሪ ኮሚቴ ሊቀ መንበር በነበረችበት ወቅት ባገኘችዉ አጋጣሚ የፀረ-ኢትዩጵያ ሃይሎች የጦር መሳርያ ማዕቀብ ሲጣስ እንደ ሊቀ መንበርነቷ አዎንታዊ ሚና ለመጫወት ፋቃደኛ አልነበረችም፡፡

ኳታር የተባበሩት መንግስታት ጊዝያዊ የፀጥታ ምክር ቤት አባል በነበረችበት ጊዜ የሶማልያ ጉዳይ በተነሳ ወቅት የኢትዩጵያ ሰራዊት ያለ ቅድመ ሁኔታ ከሶማልያ መዉጣት አለበት ብላ ሽንጧን ገትራ ስትከራከር የነበረች አገር ነች፡፡

ታድያ የምስራቅ እና አፍሪካ ቀንድ አገራት የሶማልያ ጉዳይ በዋናነት የሚመለከታቸዉ እያሉ እንዴት ተብሎ ነዉ ሶማልያ የአረብ ሊግ እና የኳታር አጀንዳ የምትሆነዉ? እዉነትም ቅኘርት ነበር፡፡የኳታር መንግስት ከዚህ ቅኘርት ነቅቶ ከኢትዩጵያ መንግስት አቋም መቀላቀሉ የሚያስመሰግነዉ ነዉ፡፡ የዘገየ ዉሳኔ ቢሆንም፡፡

ኢትዩጵያ ወዳጆች ያብዛላት! አሜን!